# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 36 ቁጥር 3 — ታኅሣሥ 2003 ዓ.ም


## <u>ግፍ በሀገር ሲናኝ፤ ኩበት ጠልቆ ድንጋይ ይዋኝ</u>

*አንዱ አገዛዝ በሌላው ሲተካ የኢትዮጵያ ሕዝብ መርገምን በመከራ ማጀብ ተገዶ ወሩ ቢቀያየርም የሰማዕትን ቀን ማክበር መገደዱ አልቀረም፡፡ የጣሊያኑ ግራዚያኒ ፍጅት ህውልትን አትርፎ የካቲት 12 ሲመጣ የሚታሰብ ሲሆን በአፄው ጊዜ ደግሞ እነጥላሁን ግዛውና በርካታ ተማሪዎች የተገደሉበት ወርሀ ታህሣሥ የሰማዕት ቀን ተብሎ በተለይ በተማሪዎች ሲከበር ቆይቷል፡፡ የደርጉና የወያኔ ፍጅቶች በመበርከታቸው የመታሰቢያ ወሮች እንደ ሁኔታውና አከባሪው ሲለያዩ ቢቆይም ህዳር ወር በብዙዎቹ ባለፈው ተከብሯል፡፡*

*ሀገራችን ኢትዮጵያ ጭራቆች እየሰፈሩባት ባጓሩ ልክ ደም እየፈሰሰ የሰማዕትና ሟች ቁጥር እየጨመረና እየበዛ እንጂ እየቀነሰ አልሄደ ብሏል፡፡ ወያኔ ሕዝብን በመፍጀት ያለፈውን አገዛዝ ሊቀድም አጥብቆ ከመወዳደሩ ባሻገር ሀገርንም ሊገድል ቆርጦ የተነሳ ነውና የከፋና በደም የከረፉ መባሉ ሲያንሰው ነው፡፡ ይህ ቢባልም በሀገራችን ታሪክ አሰቃቂ ወንጀልን በሕዝብ ላይ የፈፀመው የኮለኔል መንግሥቱ አገዛዝ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የሕዝብን ሰላማዊ ትግል ለማፈንና አምባገነንነቱን ለማስፈን ሲል የፈርጣጩ ኮለኔል አገዛዝ ቀይ ሽብርን አውጆ ብዙ መቶ ሺህ ህይወትን ማጥፋቱና ብዙሀኑን በመንፈስም በአካልም ማቁሰሉ የሚረሳ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ አረመኔው ወያኔ ወንጀለኞቹን ለመልቀቅ ደፋ ቀና ሲል ወጠጤ ለወጠጤ ቢፈርዱ እንዳይታረዱ የሚለውን የሚያስታውሰን፡፡ የወያኔ መሪዎች በድርጅት ደረጃ በቀይ ሽብሩ ቢያንስ በትግራይ የተሳተፉ ከመሆናቸው ሌላ ዛሬም ቢሆን የቀይ ሽብር ዋና ሰለባ የነበረውን ኢሕአፓን ወያኔ በጠላትነት ፈርጆ እያሳደደው ነውና ደርግና ወያኔ ጠላት ይጋራሉ፡፡ በዚህ መስክ ቢተዛዘኑ የሚገርም ሊሆን አይገባውም፡፡*

*መጪው ዘመን ምን ይመስላል ስንል ግምታችን የግድ ያለፈውን መቃኘት ይኖርበታል፡፡ ዛሬ ወንጀለኞችን ለመፍታት ሽር ጉዱን ስናይና ሀገርና ሕዝብ ላይ ግፍ ሲናኝ ድምፃቸውን ያላሰሙ የሃይማኖት መሪ ነን ባዮች ዕርቅ ወሰላምን ሊሰብኩ ሲነሱ ስንታዘብ ከማዘን አልፈን ብንቆጣ ሲያንስ ነው፡፡ በቀይ ሽብር ጊዜም የታጋይና ተኪ የለሽ ጀግኖች አስከሬን በየመንገዱ*

ተጥሎ ሲሰጣ፤ ወላጆችና ዜጎች በልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው አስከሬን ዙሪያ ቆመው ማልቀስን ተከልክለው እሰየውን ዝፈኑ ሲባሉ፤ ዛሬ ይፈቱ የሚባሉት እነቀልቤሳ፤ ኃምሳ አለቃ ተሾመ ፤ የማዕከላዊ ገራፊዎችና መርማሪዎች፤ ስማቸውን ብናውቅም በዚህ ልንጠቅስ የማንፈልጋቸው በስደት ያሉ ቀይ ሽብር አራማጆችን ሁሉ ወያኔ ምን አጠፉ ሊለን ሲነሳ በዝምታ ማለፉ አስጠያቂ ይሆንብናል:: እነተሰማ ደሬሳ፤ አንጋው ሁሴንና ስንቱን ታጋይ ላባደርና ወጣት የፈጀው ጣምያለው እሸቴ፣ መቶ አለቃ ተስፋዬ ቼንቶ፣ እርገጤ፣ ፈቃዱ፣ ገስግስ ጵጥሮስ፣ መኩሪያና ሌሎችም በስየል ስንቱን ሲያሰቃዩና የቀሰሉት ላይም በቦት ጫማቸው ይቆሙ የነበሩ አረመኔዎች ከእስር ተለቀው በከተማ ሲንፈላሰሱም በዝምታ በዜጎች መታየቱ ዜጎችን የሚያስጠይቅ ነው:: አያሌ ነፍስ ገዳዮች ዛሬ ነፃ ሊሆኑ ዝግጅት ሲጦፍ፤ አያሌ ሀገር ወዳዶችና ጀግኖች ደግሞ ድራሻቸው እንደጠፋ የሚታይ ሆኗል:: ግፍ በሀገር ሲናኝ ኩበት ጠልቆ ድንጋይ ሊዋኝ የሚያሰኝ ነው:: የተገላቢጦሽ:: ሰለባዎቹ ለእስር ሲዳረጉ ነፍሰ ገዳዮቹ ለመለቀቅ ታጭተዋል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የቀይ ሽብሩንም ታሪክ ለመበረዝና የወንጀለኞቹን ጥፋት ለመሰወር፤ ይባስ ብሎም ሰለባውን-ተጠቂውን በሽብር ለመክሰስ ሰፊ በወያኔ የታገዘ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ነው:: ሀሳዊ ምስክሮች፤ እነተኮላ ዓይነቶቹን ሰው በላ አውሬዎችና ገራፊዎች የሚያዳንቁ፤ አስመሳይ ምሁሮች በማያውቁት ገብተው የባዕዳንን ተመክሮ በግልቡ ቃኝተው ነጭ ሽብር በሚል ሊዘባርቁ የሚቃጡ፤ በድርጅቱ ይህ ነው የሚባል ሚና ባይኖራቸውም የኢሕአፓን ታሪክ አዋቂና መስካሪ ነን ብለው በሬ ወለደን የሚከትቡ፤…ወዘተ ፈልተውና ተፈልፍለው ነገር ዓለሙን እያዘባረቁና እያደፋረሱ ናቸው:: ይህ አፀያፊ የታሪክ ብረዛ እየተካሄደ ባለበት ወንጀለኞቹን መልቀቅ የተጀመረው አሳፋሪ ሂደት የሕዝብን ቁጣና ተቃውሞ መቀስቀሱ የሚጠበቅ ነው:: ፍትሕ ያጣ ደም ይጮኻልና መደመጡም የማይቀር ነው::

ከነገር ማን ይቅደም የደም ተብሏል:: ይህ የበቀል ጉዳይ አይደለም:: ወያኔ ወንጀለኞችን በዕብሪትና ህገ ወጥ መንገድ በመልቀቅ ለሰማዕትና ለሕዝብ ወገኖች ሁሉ ምን ልትሆኑ ብሎ ለመወጣጠር መሆኑ ግልፅ ነው:: ይኸው እኔ መሀሪና ከሀሊ ሆኜ ልለቃቸው ስነሳ ቂም በቀል አስተናጋጆች እነኢሕአፓ ተቃወሙ ብሎም ርካሽ ትርፍን ለማግኘትም ነው:: ኢሕአፓ ግን ስንት መቶ ሺህ አባሎቹና ደጋፊዎቹ እንዲሁም ምንም በፖለቲካው ንክኪ ያልነበራቸው ዜጎች ጭምር አልቀዋልና ይህን ፀረ ሕዝብ የወያኔ ድርጊት በዝምታ የሚያልፈው አይሆንም:: ወደፊትም ቢሆን ሊፋረድና ሕዝብ በሚፈልገውና በሚደግፈው መንገድ ብቻ ይህን ቁስል ሊያክም መጣሩ አይቀርም:: አሰቃቂውና ሀገሪቷን ያቆሰለው ሽብር ተሸፋፍኖ የሚታለፍ አይደለም:: ጥራዝ ነጠቆችና ታሪክ በራዦች እንደሚሉት፣ ኢሕአፓ በሰላም መታገል እየተቻለ ለተኩስ ተቻኩሎ ደርግ ላይ የተኮሰ ሳይሆን (ወይም "ነጭ ሽብር" የጀመረ ሳይሆን) ወታደራዊው አገዛዝ በግራ ቀኙ ሕዝብን ሲፈጅና ወንጀል ሲፈፅም ለመከላከል የተጀመረ

ያውም ውሱን የሆነ እንቅስቃሴ ነበር። ይህንን ሐቅ ክደው ሽብርተኛውን አገዛዝ ተጠቂ አድርገው በማቅረብ ዛሬም ቢሆን ኢሕአፓን ለመክሰስ የሚራወጡ ፀሐፊዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ዶክተር ፕሮፌሰር በሉን ባዮች በወያኔ በቀጥታም በእጅ አዙርም እየተደጉና እየተደጋገፉ በመንጫጫት ላይ ናቸው። ኢሕአፓ በነሐሴ 26/1967 ባሰራጨው ፕሮግራሙ ወይም መርሀ ግብሩ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተከበሩ በሰላም የሚታገል መሆኑን ያሰፈረ ከመሆኑ ሌላ በከተሞች ትጥቃዊ ትግል ማካሄድ በሚል ልዩ እስኳዶችን አሰልጥኖ ያሰማራበት ሁኔታ አልነበረም። ድርጅቱ በ1969 የራስን መከላከል እርምጃ መውሰድ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ደርግ አያሌ ግድያዎችን፤ ርሸናዎችን፤ አፈናዎችን በአዲስ አበባ፣ ጅማ፣ አዋሽ፣ አስበ ተፈሪ፣ ...ወዘተ በሲቪሎችና ወታደሮችም ላይ አካሂዷል። በዚህ ወቅት የሕዘብ ተቃውሞና ይህንንም እየመራ የነበረው ኢሕአፓ ብረት አንስቶም በከተማ አልተኮሰም ነበር። ይህም ማለት ደርግ ይህንን ርሸና፣ ግድያና አፈና ሊያካሂድ የሚያስገድደው ምንም ዓይነት ሽብር ወይም ትጥቃዊ ተቃውሞ አልነበረም። በመስከረም 1969 በይፋ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት ከማወጁ በፊትም ግድያና ርሸናውን በህብረተሰቡ ላይ ሲያካሂድ እንደነበር ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ ምስክር ነው። የኢሕአፓ የከተማ ትጥቃዊ የራስ መከላከል እንቅስቃሴ የጀመረው ደርጉ ሕዝብን እየፈጀ ባጅቶ ይህ አልበቃ ብሎት በይፋ ጦርነት አውጆ ከነፃ እርምጃ ወደ ቀይ ሽብር ሲሸጋገር ነው። ያልተበረዘው ታሪክ፣ የኮለኔሉ አገዛዝ ተቃውሞን ለማጥፋት ግድያና ሽብርን አውጆ ሕዝብ መጨረሱን ነው። የዚህ አሰቃቂ ጊዜ ዝርዝሩ ደግሞ የተመዘገበና የታወቀ ነውና የደርግ ርዝራዦች ሆኑ ወያኔዎችና ቅጥረኞቻቸው ሊደብቁት የሚችሉ አይደለም።

“በኢሕአፓ ላይ ቀይ ሽበር ልንሰድባቸው ተዘጋጅተናል። ደማቸው የፀረ አብዮት እሳትን የምናጠፋበት ውሀ ሁኖ ያገለግለናል” ብለው ባንዳ ምሁራን ሲደነፉ መንግሥቱ ደግሞ ቀይ ቀለም የተሞላባቸውን ጠርሙሶች በአደባባይ እየሰበረ አጓራ። ቀይ ሽብር ተራ ግድያ አልነበረም--አሰቃቂ ግፍና ግብረ ስየልን ያቀፈ የፍጅትና የጭካኔ ድርጊትና ሂደት ነበር። ይህን በተመለከተ ከዚህ በፊት ተፅፎ የነበረውና ቀጥሎ የምንጠቅሰው ግልፅ አድርጎ ያስረዳል፤

> *“ ቀይ ሽብር ግልፅ የሆነና የለየለት የጭፍጨፋ ጥሪ ከመሆኑም በላይ ዳር እስከ ዳርም ያዳረሰ ነበር። ወላጆች በልጆቻቸው “ጥፋት” ተረሸኑ፤ ልጆች ታላቆቻቸው በፈፀሙት “ወንጀል” ተገደሉ፤ ለሥነ ልቡናዊ ዓላማና የአንዳንድ ንክ ባለነፍጦችን ፍላጎት ለማርካ ንፁሕ ሰዎች ታረዱ። ለከት ያልነበረው በዓመፃ መጠናበዝ ታየ። ቀዩ ሽብር ማንኛውንም አካባቢ አልማረም፤ ምሕረት እርሙ ነበር። ከተልዕኮውና ከተግባር መመሪያው ሊሰርፅ የሚችለው አውሬነትና በዘፈቃደኛነት ነበርና የሽብር ዓላማው ማስደንገጥ ነው። ታዲያ ጫፍና እግሩ ከማይጨበጥ፤ የአመክንዮን ሕግ ከማይከተል፤ ማስረዳት ከማይቻል በጅምላ ከሚካሄድ አመፃ በላይ ምን ሊያስደነግጥ ይችላል?....በገልፅና በምስጢር ይካሄዱ የነበሩት ርሸናዎች ቁጥራቸው እየጨመረ*

> *ግብረ ሰዶሙም ይበልጥ እየከፋ መጣ:: ግብረ ሰዶሙን የሚጠቀሙበት ከእስረኛው ምስጢር ለማውጣት ሳይሆን እሱን ራሱንና (እሷን ራሷን) ሌሎችንም ለማሸበር፣ እንዲሁም ለበቀል መውጫ ነበር:: እሥረኞች በሌሎች ፊት በግብረ ሰዶል ይሰቃያሉ፣ እሥረኞች ጓደኞቻቸውን በግብረ ሰዶል እንዲያሰቃዩ እንዲያውም እንዲገድሉ ይደረጋሉ፣ የተቦተራረፈ የሰው አካል ሽፋን አይደረግለትም፣ሬሳ ካውራ ጎዳና ላይ ይጣላል::...የሽብር ዓላማ ቀልብን መግፈፍ ነው:: ቀይ ሽብርም የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈፀም ወደ ኋላ አላለም::”*

ቀይ ሽብር ዋናው ዓላማው ቋሚውን አሸብሮ ለማንበርከክ ነውና ህብረተሰቡን አናግቶና ከሁለት መቶ ሺ ያላነሰ ታጋይ ዜጋን ፈጅቶ አሰቃቂ ዘመንና ሁኔታን በማስፈኑ፣ ለወያኔ ሀገሪቷን አጋልጦ ሰጥቶ ዛሬ እየደረሰ ላለው ጉዳት ተጠያቂ ነው:: ቀይ ሽብርና ሕዝብን የፈጀው የደርግ ሥርዓት ነውናም በሀሰት ኢሕአፓን በመክሰስ ሽፋን ለመስጠት መሞከሩ ከንቱ ነው:: በዚሁ ሽብርም ባዕዳን በቀጥታና በእጅ አዙርም መሳተፋቸው ከቶም የሚካድ አይደለም:: በመሆኑም ያን አሰቃቂ ግድያ ያካሄዱት ዛሬም ቢሆን ያጠፋነው የለም፣ በኢሕአፓ ላይ የወሰድነውን እርምጃ በተመለከተ ፀፀት የለንም፣...ወዘተ እያሉ የሚለፍፉት እነመላኩ ተፈራ ሆኑ ዓለሙ አበበና ቀልቤሳዎችም ቢሆኑ በነፃ፣ያውም በወያኔ ምህረት ተሰጥቷቸው ሊለቀቁ የሚችሉ አይደሉም:: እነመኩሪያ፣ ፍቃደ ፣ ኃምሳ አለቃ ተሾመ፣ እርገጤና ሌሎችም ስንቱን በግብረ ሰዶል የገደሉ፣ እናትና ልጅን ሳይቀር በአንድ የደፈሩ፣ ስጋን በሳንጃ ቆርጠው ብላ ያሉና አረመኔ ግፍ የፈፀሙ ያውም አጠፋን ሳይሉ ሊለቀቁ መቸም መታሰብ የሌለበት ነው:: ወደፊት በሰላምና በዕርቅ እንጓዝ ሲባል አሻፈረኝ ሲል የከረመው ወያኔ በመጀመሪያ ደረጃ በቀይ ሽብር ጉዳይ ዳኛና ፈራጅ ሊሆን ካለመቻሉ ሌላ ምህረት ሰጪ ሊሆንም ከቶም የሚችልና የሚገባውም አይደለም:: ህብረተሰቡ ቁስሉ ይሻል፣ ቂም በቀሉም ይጥፋ ቢባል እንኳን ይህን ምህረት የሚያደርገው ሕዝብ ነው:: በተለይም በደሉ የደረሰበት ሕዝብ:: በደቡብ አፍሪቃ ተካሄደ የተባለው የሐቅ ፍለጋና የዕርቅ ሂደት በቅድሚያ የሕዝብ መንግሥት መመስረትን የጠየቀ መሆኑም ይታወሳልና በኢትዮጵያም ከቀይ ሽብር ወንጀለኞች ጋር ዕርቅ ይደረግ ከተባለ በቅድሚያ ወንጀላቸውን አምነው ለወያኔ ካድሬ-ጳጳሰ ማመን ሳይሆን ከሕዝብ በይፋ ምህረትን መጠየቅ ይኖርባቸዋል:: በኢትዮጵያም ሕዝብ የመረጠውና ያመነው ከወንጀል ነፃ የሆነ መንግሥት መመሥረቱ መቅደም አለበት:: ታሪኩ ሳይደበቅና ሳይሸፋፈን በግልፅ ወጥቶ ወንጀለኞቹም ሁሉ ጥፋታቸውን አምነው ሂደቱ በዚህ መልክ ከተካሄደ ለአሁኑም ሆነ ለመጭው ትውልድም ትምህርታዊ ሆኖ ሊጠቅም ይችላል:: ወያኔ ዛሬ ከደርግ ባልተናነሰ ግብረ ሰዶል እየፈፀመና አፈናም እያካሄደ ነውና ሌሎችን ሊዳኝ ሆኖ ሊቀጣ የሞራል ብቃት እንደሌለው ኢሕአፓ ገና በ1983 አቅርቦ እንደነበርም አይረሳም::

ሀገርን ወደ ዴሞክራሲና ወደ ዕድገት ለመውሰድ መሣሪያውና መንገዱ ፍጅት አለመሆኑ በታሪክም የታወቀ ቢሆን በቀይ ሽብሩም ተጋልጧል:: ዛሬም የመለስ አገዛዝ የሽፍንፍን ሽብርን

እያካሄደ ለመግዛት የሚያደርገው ሙከራ የሚያዋጣው አለመሆኑ ውሎ አድሮም ለከፋ ውደቀትም እንደሚወስደው አረጋጋጭ ነው:: ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስረሳ ሆኖ ዛሬ በወያኔ ላይ ትኩረቱ ያለፈውን ያስረሳ ቢመስልም ለፍትህ የሚጮኸው የንፁሃን ዜጎች ደም፤ የቀይ ሽብር ሰማዕት ደም ከነጎድጓድ በላይ ይጮኻል፤ ይጮህብናል:: ለዚህ ጩኸት ዕረፍት ሳንሰጥ፤ ማሳረጊያ ሳንለግስ በሀገራችን ዕርቅና ሰላምን አስፍኖ በጋራ መኳዙ አስቸጋሪ ይሆናል:: የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ከፊሎቹ ቢታሰሩም በርካታዎቹ ደግሞ--ከአረመኔው ኮለኔል ጀምሮ-- በምቾት ስደት ላይ አሉ:: በርካታዎቹ በየድርጅቱ --በወያኔም ውስጥ ሆነ ተቃዋሚ ነን በሚሉቱም ውስጥ-- ቅንጣት ይቅርታን ከሕዝብ ሳይጠይቁ ተሰግስገውና መሪ በሉን እያሉም አሉ:: ይህ ደግሞ የሀገራችንን ምፀት ቀጣይ የሚያደርግ ነውና ማብቃት ያለበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: አርበኞችን ለስቅላት ዳራጊና ባንዳ ሿሚ አገዛዝ የተወልን ቅርስ ፀያፍ ነውና የመጣውን አገዛዝ ሁሉ የሚያገለግሉ፤ ወንጀል የሚፈፅሙ፤ ገራፊና ግብረ ስየል ፈፃሚ የሚሆኑ በርክተዋል:: በግ አንኳን ሲቀላቀል ባ ይላል የተባለው ተረስቶ ከደርግም ከወያኔም ተለጥፎ ስንት ወንጀል የፈፀመው ሁሉ ሳይሆንለት ሰልፍ ቀይሮ--ግን መቸም አጥፍቼ ነበር ሳይል-- የሕዝብ ጎራ ውስጥ ሲርመሰመስ ማየት በዝቶብናል:: ይባስ ብለው ይህን ዓይነት አድርባዮችና ወንጀለኞች የፈረደበት ኢሕአፓ ላይ በየጥሻው ገብተው ውግዘትን ማዝነባቸው ነው:: ሕዝብ ይቅርታ ይጠየቅ፤ ማረን ይባል: ወንጀለኛውም አጠፋሁ ተፀፀትኩ ይበል በሚል ደግመን ደጋግመን የምንወተውተው ያልሻረ ቁስላችን በሚመግበው የቂም በቀል ስሜት በመነሳሳት ሳይሆን ፀፀት አልባ ወንጀለኛንና ገዳይን ማቀፉ ሞኝ ሰው ሁለት ጊዜ ያለቅሳል እንዳይሆንብን ነው:: ወያኔን በሚገባው መንገድም ለመታገል ይህን ትግል በዚህም በዚያም የሚያዳክሙትንም ከመድረኩ ማራቅ አስፈላጊ ነው::

ወጣት ሽማግሌ፣ ባልቴት አዛውንት፣ የተማረ ያልተማረ፣ ነጋዴ፣ ሽቃይ፣ ሲቪል ወታደር፣ ከተሜ ባላገር፣ ሴት ወንድ፣...በመሠረቱ ብሔረሰብ ሳይለይ የመንግሥቱ አገዛዝ ዜጎችን በጅምላና በገፍ ጨፍጭፏል:: ሕብረ ብሔራዊ ድርጅቶችን በተለይም ኢሕአፓን በማጥቃት ደግሞ ለገንጣዮች መጠናከር በር ከፍቷል:: ሰፊውን የወንጀል ዝርዝር በዚህ ማቅረቡ ባያመችም ያ የቀይ ሽብር አገዛዝ ሀገርና ሕዝብን መጉዳቱንና ለውድቀት መዳረጉን ግን ከቶም መካድ የሚቻል አይደለም:: ዛሬ እንዴት ለወያኔ አረመኔ መንጋ ተጋለጥን ብለን መመርምር ሲገባን፤ ምርምሩም ለዚህ መጋለጥ ተጠያቂው ያ ወታደራዊ አገዛዝ መሆኑን ያሳየናል:: አንዳንዶች ያ አገዛዝ ሀገር ወዳድ ነበር ወያኔ ግን ፀረ ኢትዮጵያ ነው ሲሉ በእርግጥም ሁሉንም ጨቋኝ ሥርዓት አንድ ማድረጉ ስህተት ቢሆንም ሀገርን ወዶ ሕዝብን ግን ጨርሶ የሚል ፈሊጥን ልንቀበልና ልናስተናግድ አንችልም፤ አይገባንምም:: ወያኔ በበኩሉ ይህን የምሕረት እርምጃ ልወስድ ተነሳሁ የሚለው ለራሱ የፖለቲካ ትርፍ መሆኑ ግልፅ ከመሆኑ በላይ የፖለቲካ እስረኞችን አብዮቱ የመጣባቸው ብሎ ሲያወግዝ የቆየው የወያኔ ካድሬ--ጳጳስ ዛሬ በተዓምር ምሕረትና ዕርቅን ጠያቂ መሆኑ በራሱ አነጋጋሪ ነው:: የወያኔን መሰሪ ዓላማ አጋላጭ ነው::

ለዚህም ነው በዚህ ወያኔያው ቧልት መግባቱን መሳተፉን የምናስበውም አይሆንም የምንለው:: ለዚህም ነው የሽማግሌዎች ኮሚቴ በሚል ሽፋን የወያኔን ግብ ሊረዱ የተኮለኮሉትንም ስንቃወም የቆየነው:: እነዚህ አስታራቂ ነን ባይ አዛውንት ለወያኔ ፖለቲካ ውጥረት ማርገቢያ የተወሰኑ ድርጅቶች መሪዎችን ሲያስለቅቁ አንድም ቀን በ1997 ታፍሰው-ታስረው መከራና ፍዳ የሚቀበሉትን ሆነ በወያኔ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋውን የኢሕአፓ መሪዎችና አባላት በተመለከተ አንዲትም ቀን ትንፍሽ ሲሉ አልተደመጡም:: ለዚህም ነው ይህ የወያኔ የምሕረት እንቅስቃሴና ሂደት የፖለቲካ ውንብድናና ማጭበርበር ሆኖ የሚገኘው::

በሀገራችን የቀይ ሽብር ዳግም ክስተት እንዳይታይ የነበረን ምኞት ከንቱ ቀርቷል:: የወያኔ አገዛዝ ፍጅትና ግብረ ስየልን፣ ኢፍተሀዊነትንና ዘረኝነትን አክሎበት ቀጥሎበታል:: ደምን የማይጠይቅ የዕርቅ ሂደት ይኖር ዘንድ የነበረው ምኞት ተኗል:: የወያኔ አገዛዝን ለመጣል ደም መፍሰሱ የግድ ነው--ወያኔ የንፁህ ዜጎችን ደም ማፍሰሱን ቀጥሏልና:: የሕዝብ መንግሥት ገና አልተመሰረተምናም፣ የቀይ ሽብር ወንጀለኞች ያጠፉነው የለም ባይ ናቸውና፣ ምሕረት ሰጪው ሕዝብ መብቱን አስከብሮ በነፃ በሚወስደው መንገድና ውሳኔ ሳይሆን በፀረ ሕዝቡ ወያኔ ነውና ዕርቅም ምሕረትም የዛሬ አይደሉም:: በቅድሚያ የነፍሰ ገዳዩ ወያኔ አገዛዝ መወገድ አለበት:: እስከዚያው ግን ቀደም እንዳልነው መቸስ ምን ይደረጋል ነውና ለቀይሽብሩ መስተጋብራን ሆነ ለወያኔም በአንድ አብዮታዊ ገጣሚ የተላለፈውን መልዕክት ከልባቸው ቢጥፉት የሚበጃቸው ይሆናል፤

*" በሚቀጥለው ዙር በመጪው ጊዜያት*
*ተዉት አትድከሙ ይብቃ የናንተ ምጣት*
*በድቅድቅ ጨለማ በደረቁ ውድቅት*
*መዝጊያዎቻችንን ለመስበር ለማንኮት*
*እኛ ነን ምንመጣ ተንግዲህ አታክቱ*
*ቢሻን በማለዳ ቢሻን በሌሊቱ*
*ለናንተውም መዝጊያ ይድረሰው ረደዔቱ::"*

ቀይ ሽብርም ሆነ ወያኔያዊ ሽብር የሕዝብን የትግል መንፈስና ሀገር ወዳድነት ለአንዴም ለሁሌም ማጥፋት አልቻለም፣ አይችልምም:: ይውደም የተባለውና አሁንም ጣሉት ተብሎ የሚሳደደውም ኢሕአፓ በሰማዕት ደም እየተደገፈ በትግል የሚቀጥል የሕዝብ ድርጅት ነው:: ወንጀለኛ ሌላውን ወንጀለኛ ቢለቅ ሆነ ቢተቃቀፉ ይህን ሐቅ አይለውጠውም::

ወንጀለኞች ለሕዝባዊ ፍርድ ይቀርባሉ!
ፀረ ሕዝቡ የወያኔ አገዛዝ በሕዘባዊ ትግል ይወገዳል!
ክብር ለሰማዕታት!